ይህን ፒዲኤፍ ከwww.jw.org/am ላይ ማውረድ ትችላለህ

# ምሥራቹን የሚያካፍሉ ሰዎች የሚያገኙት እርዳታ

**ራእይ 14:6, 7ን አንብብ።** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን “ምሥራች” “ለብሔር፣ ለነገድ፣ ለቋንቋና ለሕዝብ ሁሉ” ስንሰብክ ይሖዋ፣ እኛን ለመርዳት መላእክቱን ይልካል። የjw.org/amን መነሻ ገጽ በመጠቀም ከእነዚህ ብሔራት፣ ነገዶች፣ ቋንቋዎችና ሕዝቦች መካከል ስለ አንዳንዶቹ ማወቅ ትችላለህ።

በመነሻ ገጹ ላይ ከላይ የሚገኘውን እያንዳንዱን ፎቶግራፍ በቤተሰብ ተመልከቱ። በፎቶግራፉ ላይ የሚታየውን አገር ለመገመት ሞክሩ። ከዚያም “ክፈት” የሚለውን ጠቅ በማድረግ የሰጣችሁት መልስ ትክክል መሆኑን አረጋግጡ፤ እንዲሁም በዚያ አገር መጽሐፍ ቅዱስን የሚያስተምሩት የይሖዋ ምሥክሮች ቁጥር ስንት እንደሆነ ተመልከቱ። ከዚያም ከሥር ያለውን ካርታ ተመልከቱ። አገሩ የሚገኝበት ቦታ ላይ ምልክት አድርጉ፤ እናንተ ከምትኖሩበት አገር ምን ያህል ይርቃል?

▶ **አሁን ደግሞ እንዲህ አድርግ፦** *የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የኢንተርኔት ቤተ መጻሕፍትን* ተጠቅመህ በመነሻ ገጹ ላይ ስለተጠቀሰው አገር ምርምር ለማድረግ ሞክር። (“**የሕትመት ውጤቶች > የኢንተርኔት ቤተ መጻሕፍት**” በሚለው ሥር ይገኛል።) *የ2013 የይሖዋ ምሥክሮች የዓመት መጽሐፍን* (በአማርኛ አይገኝም) በመጠቀም *አንተ* በምትኖርበት አገር ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያስተምሩት የይሖዋ ምሥክሮች ቁጥር ስንት እንደሆነ ለማወቅ ሞክር። (“**የሕትመት ውጤቶች > መጻሕፍትና ብሮሹሮች**” የሚለውን ክፈት፤ ከዚያም *የዓመት መጽሐፉ* ከሚዘጋጅባቸው ቋንቋዎች አንዱን [ለምሳሌ እንግሊዝኛ] ምረጥ።)



www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania